# ኦሮሞ በገዛ ሃገሩ ላይ ክብሩ የሚዋረደው ለርሱ የቆመለት መንግስት ስለሌለው ነው

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣን መንበር ላይ ሲፈራረቁ የኖሩ ገዢዎች ሁሉ ለኦሮሞ ህዝብ በጎ የዋሉለት ጊዜ በታሪክ ኣልታየም። ኦሮሞ በብሄሩ ብዙህነት፣ በመሬቱ ስፋትና በበለጸገው ሃብቱ ምክንያት በገዛ ሃገሩ ላይ ሰላም ተነፍጎ ይኖራል። ለቆዳዋ ሲባል እንደምትገደል ጉሬዛ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ገዢ ሁሉ ይታደናል። የቀደሙት የኢትዮጵያ ገዢዎች በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያደረሱትን በደል ለታሪክ ትተን የዛሬው ባለ ጊዜ በሆነው በወያኔ ስርኣት ስር ህዝቡን የገጠሙትን ችግሮች ማንሳት ኣስፈላጊ ነው።

የወያኔ መንግስት በብሄር ማንነት ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ ስርኣት ዘርግቻለሁ በሚል ሽፋን በኦሮሞ ህዝብ ላይ በሁሉም ማእዘናት የጥቃት ዘመቻ ከፍቶ የማዋከብ ፖሊሲውን ገቢራዊ እያደረገው ይገኛል። ለረጅም ዘመናት በፍቅርና በመከባበር ኣብረው የኖሩትን ብሄር ብሄረሰቦችን ኣንዱን በሌላኛው ላይ በማነሳሳት የስልጣን እድሜውን ማራዘም ይፈልጋል። በተለይም የኦሮሞ ኣጎራባች ብሄር ብሄረሰብ ተወላጆችን ሆን ብሎ በማሳሳት እያስታጠቀ በሁሉም ኣቅጣጫ ኦሮሞን እንዲወጉ የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። ወያኔ ህወሃት የሃገሪቱን የፖለቲካ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ወቅት ኣንስቶ ተከሰቱ በሚባሉት የብሄር ብሄርሰቦች ግጭት ሁሉ ውስጥ በተደጋጋሚ የኦሮሞ ስም የሚነሳውም ለዚሁ ነው። ኦሮሞ ለጎሮቤቶቹ ህዝቦች ሰላማዊ ህይወት ኣስጊ ሃይል ሆኖ ሳይሆን የወያኔ ትንኮሳ በኣብዛኛው ኦሮሞው ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ብቻ ነው። ኣንዳንዶቹን በምሳሌ እያነሱ ማየት የግድ ይላል።

በምእራቡ በኩል ወያኔ የጉሙዝ ብሄረሰብ ተወላጅ የሆኑ ግለሰቦችን ኣያሰለጠነና እያስታጠቀ ኣጎራባች በሆኑ ሲቪል የኦሮሞ ነዋሪዎች ቀዬ ላይ ኣሰማርቶ ለመቶዎች ህወይት መጥፋትና በሚሊዮኖች ብር ለሚገመት የንብረት ውድመት ምክንያት ሆኗል። ኣሁንም ከዚህ እኩይ ድርጊቱ ኣልተገታም። በምስራቅ እንደ ኢሳ ያሉ የሶማሊ ጎሳዎችን ለረጅም ጊዜ እያስታጠቀ በሰላም በቀዬው ላይ ሰርቶ ለመኖር ደፋ ቀና በሚለው የኦሮሞ ነዋሪ ላይ ወረራ ያስፈጽማል። የኦሮሞ ተወላጆችን መግደልና ማስገደል፣ ህፃናትን መድፈርና ማስደፈር፣ የኦሮሞን ሃብት ንብረት መዝረፍና ማስዘረፍ እንዲሁም በታሪክ የሚታወቀውን የኦሮሞ መሬት ቆርሶ ለኣጎራባች ብሄረሰቦች በመስጠትና የራሳቸውን ባንዲራ ኣንዲያውለበልቡበት በማድረግ ትንኮሳ መፍጠር መንግስት ነኝ ከሚለው ከዚህ ነውረኛ ቡድን ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በደቡብ ኦሮምያ የሚታየው እውነታም ተመሳሳይ ነው። የቦረናው ኦሮሞ በኣያት ቅደመ ኣያቱ ቀዬ ላይ ጎጆው ተቃጥሎበታል። ከብቶቹ በገፍ ተዘርፈዋል። ከዚሁ ሁሉም ኣልፎ እትብቱ የተቀበረበት መሬቱ በሃይል ተወስዶ ለሌሎች ተሰጥቷል። የጉጂ ኦሮሞ እጣም ከዚህ የተለየ ኣይደለም። ደቡብ ኦሮምያ ውስጥ "በግጦሽና ውሃ ይገባኛል የተነሳ ግጭት" በሚል ሽፋን በተለያዩ ጊዜያት ወያኔ ሆን ብሎ የኣንዳንድ ኣጎራባች ብሄረሰብ ተወላጆችን በጥቅም እየደለለ በማስታጠቅ የክፉ ቀን ደራሻቸው በሆነው የኦሮሞ ነዋሪ ላይ ያነሳሳል። በመሰል የወያኔ ትንኮሳ በተጫሩት ግጭቶች ባለፉት ሃያ ሁለት ኣመታት ጊዜ ውስጥ የጠፋው የሰው ህይወት በሺዎች የሚገመት ነው። በተቀሩት የኦሮምያ ኣካባቢዎችም ቢሆን ኦሮሞው በቀዬው ላይ በሰላምና መረጋጋት መኖር ኣልቻለም።

የወያኔ መንግስት በኦሮሞ ላይ ሆን ብሎ ጠላት ለማበራከት የተነሳበት ምክንያት ይታወቃል። ትልቁ ስጋቱ የኦሮሞ ህዝብ ብዙህነት ነው። ስለሆነም ይህ ህዝብ ባንድ ጊዜ በጋራ ተነቃንቆ ብዙህነቱን ወደ ሃይል በመለወጥ የሃገሩ ኦሮምያ ባለቤት እንዳይሆን ለማድረግ ካለው ህልም የተነሳ በሰሜን ደቡብ፣ በምስራቅ ምእራብ የግጭት እሳት እየለኮሰበት ፋታ ይነሳዋል። በጥቅሉ ሲታይ ትልቁ የወያኔ ኣላማ ኦሮሞ ሃይል እንዳይሆን ማደናቀፍ ነው። ኦሮሞ ሃይል ሆኖ ከወጣ ቀንና ለሊት የሚዘርፈው የኦሮምያ ሃብት ከእጁ ይወጣል። ኦሮሞ ሃይል ከሆነ በሃይል ከያዘው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣን ተገፍትሮ ይወድቃል። ኦሮሞ ሃይል ከሆነ

የለመደው የቅንጦት ህይወት ይቀርበታል። ኦሮሞ ሃይል ከሆነ በወያኔ የተገፉ የተቀሩትን የሃገሪቷ ህዝቦችን አቅፎ ደግፎ በጋራ በመንቀሳቀስ ለወራሪነት አገዛዙ ፍፃሜ ያበጃል። ለዚህም ሲባል ነው ወያኔ ከሁሉም በበለጠ መልኩ የከረረ የጠላትነት በትሩን በኦሮሞ ላይ በማሳረፍ የቻለውን ያህል ራሱ እየመታ ባልተቻለለት ሁኔታ ደግሞ የአጎራባች ብሄረሰብ ተወላጆችን እያስታጠቀ የሚያስመታው።

ከሁሉም በከፋ መልኩ ደግሞ ባሁኑ ጊዜ በምስራቅ ኦሮምያ የሚስተዋለው ወያኔያዊ ድርጊት ከወሰን አልፎ አሳሳቢ አደጋ አርግዞ የሚገኝ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። የወያኔ ስርኣት ሆን ብሎ በሶማሊ ክልል ያሰለጠነውንና ከባድ መሳሪያ ያስታጠቀውን "ልዩ ሃይል" የተሰኘ ጦሩን እንዲሁም በአካባቢው የሚኖሩ የሶማሊ ጎሳ ተወላጆችን አስታጥቆ ኦሮሞውን በቀዬው ላይ ኢያዋከበ ይገኛል። ከቀዬው ላይም እያፈናቀለው ሜዳ ላይ መበተንም ተያይዞአል። ወያኔ ከአስርት ኣመታት በፊት ከሶማሊያ የተሰማውን የኣካባቢውን መሬቶች የመውረር ጥማት ማሟላት በሚመስል መልኩ "ታላቁዋ ሶማሊያ" የሚለው ህልም ዛሬም ከኣእምሮኣቸው ያልተፋቀ ወገኖችን በመያዝ የኦሮሞን መሬት ከኦሮሞ እጅ ፈልቅቆ ለማውጣት ዘምቶ እያዘመተ ነው። ከሶማሊ ጎሳዎች መካከል በቀላሉ የሚታለሉለትን እያስታጠቀ የኦሮሞ ነዋሪዎችን መንደር ማቃጠል፣ ሃብት ንብረታቸውን በገፍ መዝረፍና የኦሮሞን ኣንጡራ መሬት በመንጠቅ ዘመቻ ላይ ኣሰማርቷል። የምስራቁ የኦሮምያ ህዝብ ለዘመናት ባልተቋዋረጠው በዚህ ኣይን ያወጣ የወያኔ ጠላታዊ ዘመቻ እምባውን ጨርሶ ደም እያነባ ነው ቢባል ማጋነን ኣይሆንም። ይህ ብሶት ደግሞ የምስራቁ የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የመላው ኦሮምያ ብሶት ነው። ምስራቅ ኦሮምያ ውስጥ ይህን የመሰለው ገደብ ኣልባ ግፍ በወያኔ ኣደራጅነት፣ ኣሰልጣኝነትና ኣስታጣቂነት በኦሮሞ ህዝብ ላይ መተግበር ከጀመረ ኣንድም ሳይቋዋረጥ መንፈቅ ኣመት ኣልፎታል።

በተደራጀ መልኩ ታጥቆ በዘመተበት ሃይል ከቀዬው የሚፈናቀለው ኦሮሞው ኣቤት የሚልበት የመንግስት ኣካል የለውም። ምክንያቱም ኣለ የሚባለው መንግስት በርሱ ላይ የቆመ እንጂ ለርሱ የቆመ ኣይደለምና። የቀረበለት ብቸኛ ኣማራጭ ቢኖር በኣያት ቅደመ ኣያቱ የኖረበትን ኣንጡራ መሬቱን ለወራሪዎች ለቆ መሰደድ ኣልያም ባዶ እጁን እስከ ኣፍንጫው ከታጠቀ ጠላት ኣፈ ሙዝ ስር ቆሞ መሞት ሆኗል። ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ሁሉም ህዝቦች በወያኔ ፈላጭ ቆራጭ ኣገዛዝ ስር የሚገኙ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ እንደ ኦሮሞ ህዝብ የገዛ መሬቱ የምድር ላይ ሲኦል የሆነበት ህዝብ ያለ ኣይመስልም። ለዚህም ነው እንግዲህ የኦሮሞ ህዝብ የሚገኝበት የፖለቲካ ሰቆቃ በእጅጉ የመረረና የተለየ መፍትሄ የሚፈልግ መሆኑ በተደጋጋሚ የሚነገረው።

የወያኔ መንግስት ለኦሮሞ ህዝብ ያለውን ጥልቅ ጥላቻ መረዳት ያልቻሉ ኣንዳንድ የዋህ ወገኖች ይህን ችግር ማስቆም የነበረበት የመንግስቱ ኣካል ነኝ፣ ለኦሮሞ ህዝብም ቆሚያለሁ የሚለው ኦፒዲኦ ነው ሊሉ ይችላሉ። ለንደዚህ ኣይነቱ ጥያቄ ያለው ምላሽም ግልጽና ኣጭር ነው። ኦፒዲኦ ውስጥ የተሰለፉ ብሄረተኛ የኦሮሞ ተወላጆች ኣይደለም ለኦሮሞ ህዝብ መብት ተከራክረው የህዝቡን ክብር ማስጠበቅ ለራሳቸውም የድርጅት ኣባልነት መብትም ሆነ ክብር የላቸውም። ኦሮሞ ያልሆኑቱ ደግሞ እንደዚህ ኣይነቱን ጸረ ኦሮሞ ዘመቻ ለማሳካት የተሰለፉ ስለሆነ ኣላማቸውን ከወያኔ ጋር ሆነው እያስፈጸሙ ናቸው። ኦፒዲኦ የተመሰረተበት ኣላማም ለኦሮሞ ህዝብ ክብርና ልእልና እንዲቆም ሳይሆን በኦሮሞው ላይ የጭቆና ኣገዛዝን ለማራዘም ኣንዲረዳ ተብሎ ነው። ኦሮሞ ባልሆኑት ኣፋን ኦሮሞ ተናጋሪዎች የሚመራው ኦፒዲኦ ኦሮሞው ሲገረፍ ኣለንጋ፣ ኦሮሞው ሲወጋ ጦር፣ ኦሮሞው ሲረሸን ጥይት፣ ኦሮሞው ሲሰቀል ገመድ፣ የኦሮሞው መንደር ሲቃጠል እሳት ሆኖ ለጠላት ማገልገል ብቻ ነው። ከዚህ ባለፈ ኣንድም ቀን የኦሮሞ ህዝብ ቁስል ተሰምቶት የሚከራከርበት ጀግንነት ኣሳይቶ በታሪክ ኣይታወቅም። ኣንዳንድ በኦፒዲኦ ውስጥ በኣባልነት የታቀፉ የዋህ የኦሮሞ ተወላጆች

በዚህ ጉዳይ ቢንገበገቡም ለውጥ የሚያስገኝ እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ስለሌላቸው ዝምታን ይመርጣሉ። ይህ ደግሞ እየፈሰሰ ያለውን የኦሮሞ ህዝብ እንባ አያብስም፣ ቁስሉንም አያሽርም። ይህ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየፈጸመ የሚገኘውን ወደር አልባ ወንጀል እያዩ ዝምታን በመምረጣቸው ደግሞ የስርአቱ አካል የሆንን የኦሮሞ ተወላጆች ነን የሚሉት ወገኖች ነገ ከታሪክ ተጠያቂነት አያመልጡም።

የኦሮሞ ህዝብ አሁን የቀረለት አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው። ባለበት መንደር ሁሉ ተደራጅቶ ከእንደዚህ አይነቱ የጥቃት ዘመቻ ራሱን መከላከል። በቀዬው ላይ የመጣበትን የጥቃት ዘመቻ እየመከተ መሞት እንጂ ተንበርክኮ መለማመጥ የጠላትን ሆድ አያባባለትም። የኦሮሞ ህዝብ በሰሜንም ሆነ በደቡብ፣ በምስራቅም ሆነ በምእራብ እንዲሁም በማእከላዊ ኦሮምያ ባለበት ቀበሌ ሁሉ ታጥቆ እየዘመተበት ሰላሙን የሚያደፈርሰውን፣ ሃብት ንብረቱን የሚዘርፈውንና ከቀዬው ላይ የሚያፈናቅለውን ሃይል ኡኡ ብሎ በመረባረብ በጋራ ክንድ መክቶ ክብሩን ማስጠበቅ የግድ ይሆናል። በተቻለለት አቅም ተደራጅቶ ከኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ጎን በመሰለፍ ለነጻነቱና ለክብሩ መዋደቅ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው። ባዶ እጅ ሆኖ ከታጠቀ ሃይል ጋር መተናነቁ የሚያስከፍለው መስዋእትነት በእጅጉ ውድ ሊሆን ይችላል። በሃይል የሚደፈረውን ክብሩን በሃይል ከመከላከል ውጭ ሌላ አማራጭ በታጣበት ወቅት ደግሞ በዚህ መልኩ የሚከፈለው መስዋእትነት ያለ ዋጋ አይቀርምና ከመዋረድ ታግሎ በክብር መውደቅ ተመራጭ ነው።

የኦሮሞ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ የሚታወቀው በእንግዳ ተቀባይነቱ፣ በማህበራዊ ህይወት አድማቂነቱ፣ እንዲሁም በሰላምና ዴሞክራሲ ተምሳሌትነቱ በመሆኑ ከጎሮቤቶቹ ጋር ሁሉ በፍቅርና በደስታ አብሮ ኖሯል። ዛሬም በዚሁ መልኩ አብሮ መኖርን ይመኛል። የወያኔ መንግስት ግን ከቀደሙት ስርአቶች ሁሉ በከፋ መልኩ ኦሮሞን ደመኛ ጠላት በማድረግ በሁሉም ማኣዘን ጦርነት እየከፈተበት የህዝቡን መልካም ታሪክ ለማስቀየር ሌት ተቀን ኣየሰራ ይገኛል። ለዚህ ወንጀሉ ደግሞ አንድ ቀን ለፍርድ ቀርቦ መጠየቁ እንደማይቀር ጉዳይ ይሆናል።

የኦሮምያ አጎራባችና ኦሮምያ ውስጥ የራሳቸው አሰፋፈር ያላቸው ብሄረሰቦች እንዲሁም በተለያዩ የህይወት አጋጣሚዎች ኦሮምያ ውስጥ ለዘመናት የኖሩና የሚኖሩ ወገኖች በሙሉ አንድ ማወቅ ያለባቸው አንገብጋቢ ጉዳይ አለ። ዛሬ በጊዜያዊ ጥቅም ተደልለው ወያኔን በማስበለጥ ስርአቱ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚፈፅመውን ግፍ በመደገፍ ከጎኑ ቆመው ኦሮሞን መውጋት በኦሮምያ ውስጥ የወደፊት እድላቸውን ከማጨፍገግ በስተቀር የዘላለም ተድላ ሊፈጥራላቸው አይችልም። ከወያኔ ጋር የሚፈጥሩት የፖለቲካ ሽርክና ነገ ይከስማል። ከኦሮሞ ጋር ያላቸው ጉርብትና ደግሞ ተወደደም ተጠላም ለዘላለም ይኖራል። ወያኔ ጊዜያዊ ጥቅሙ ከተሟላለት በሁዋላ ዛሬ እንደ መሳሪያ የሚጠቀምባቸውን ወገኖች ነገ ዞር ብሎ አያያቸውም። እንዲያውም ነገ ለሚቀጥለው አዲስ ጥቅሙ ሲል እነርሱን መልሶ ጠላቱ አድርጎ እንደሚያስመታቸው አስቀድመው መገመት አለባቸው። ወያኔ የሁሉም የጋራ ጠላት እንደመሆኑ መጠን ዛሬ ለአንዱ የወገነ በመምሰል ሌላውን ሲያስመታ ነገ ደግሞ የተገላቢጦሹን ከመፈፀም ወደ ሁዋላ የማይል ሃፍረተ ቢስና ሃላፊነት የማይሰማው ቡድን ነው።

ስለሆነም ከኦሮሞ ጋር የዘመናት መልካም ጉርብትና ታሪክ ያላቸው ብሄሮችም ሆኑ ብሄረሰቦች አልያም ግለሰቦች በወያኔ ተደልለው የኦሮሞን ሰላም ከማደፍረስ በንቃት መቆጠብ እንዳለባቸው አበክረን ማስታወስ እንወዳለን። እንደ ተጨቋኞች ህዝቦች የሚያዋጣን ነገር ቢኖር የተባበረ ክንዳችንን የጋራ ጠላታችን በሆነው ወያኔ ላይ ማንሳት እንጂ አንዳችን በሌላኛችን ላይ መነሳሳት አይደለም። ይህ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የወያኔን ፍላጎት

ማርካትና ለዘላለም የጭቆና ኣገዛዙን እንዲቀጥል መተባበር ነው። ዛሬ ለጊዜያዊ ጥቅም እያሉ ከወያኔ ጋር በማበር ኦሮሞን በማዋከብ ዘመቻ ላይ የሚሳተፉት ሁሉ ነገ የወያኔ ጀምበር ስትጠልቅ ለፍርድ መቅረባቸው ኣይቀሬ መሆኑን ማስታወስ ይበኛል።

የኦሮሞ ህዝብም ዛሬ ትጥቅ ኣልባ በመሆኑ በገዛ ቀዬውና ሃገሩ ላይ እንደተዋረደ ለዘላለም ኣይኖርም። ተደራጅቶ በመታጠቅ የኣንድነት ክንዱን በጨካኝ

ገዢ ቡድን ላይ ያነሳል። እስከ ቀዬው ድረስ መጥተውበት ሰላም ለነሱት ሁሉ የሚገባቸውን ዋጋ መክፈሉ ኣይቀሬ ነው። ያኔ ታሪክ ለሚያቀርበው ጥያቄ ምላሽ መስጠት ያባት ይሆናል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ

ግንቦት 11, 2013